# የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (SOCEPP) ሊቀመንበር የአቶ ዓሊ ሁሴን የሥራ ቆይታ በስዊድን አገር

አቶ ዓሊ ሁሴን በስቶክሆልም ከተማ በቆዩበት የአንድ ሳምንት ጊዜ በኢትዮጵያ ሀገራችን ስላለው አስከፊ የሰብዓዊ መብት ረገጣ፤ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ከቀን እቀን እየተፈፀመባቸው ስላለው አሰቃቂና አሳፋሪ ድርጊት፣ በተለይም የወያኔ አስከፊ ቆራጭ ፈላጭ ቡድን የኢትዮጵያን ህዝብ በሃይማኖት፣ በጎሳ፣ በሥራ መስክ ወ.ዘ.ተ. እርስ በርስ ለማፋጀት ብሎም የግፍ አገዛዙን ለማራዘም በየዕለቱ የሚሸርበውን ደባና ሤራ ኢትዮጵያውያን በጋራና በተባበረ ትግላቸው እንዲቋቋሙ አሳስበዋል።



በተለይም የእስልምና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ያነሱት የመብት ጥያቄ በትክክለኛ መልኩ ግንዛቤ እንዳያገኝ፣ በውጭ አገር ጭምር ወያኔያዊው ፀረ መብትና ፀረ ኢትዮጵያዊው ቡድን በሚሊዮን የሚቆጠር ብር እያፈሰሰ ለመከፋፈል እያደረገ ያለው ሤራ በፍጥነት እንዲጋለጥ፣ ክርስቲያኑና እስላሙ የተቀረውም የህብረተሰቡ ክፍል በአንድነት ተጣምረው ለመብታቸው በጋራ እንዲቆሙ አበክረው አስረድተዋል። በስዊድን አገር ነዋሪ የሆኑ የእስልምና እምነት ተከታይ ወገኖቻችን ባደረጉላቸው ጥሪ መሠረት በሰብሰባቸው ላይ በመገኘት አገራችን በአጠቃላይ ስላለባት ችግር ጥልቀት ባለው መንገድ ከተወያዩ በኋላ SOCEPPን የበለጠ ለማጠናከር ከሁሉም የተውጣጣ ኮሚቴ በማቋቋም

በጋራ ስለፖለቲካ እስረኞችና ስለሰብዓዊ መብት መከበር ያላሳለሰ ትግል ለማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሰዋል።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ አቶ ዓሊ ስዊድን አገር የመጡበት ጊዜ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው የኢትዮጵያን አዲስ ዓመት በዓልን በሚያከብሩበት ወቅት ስለነበር በተደረገላቸው ጥሪ ላይ በመገኘት የወያኔን ግፈኛ አገዛዝ ሴራና መከፋፈል በሚገባ ለመቆቋም የእስልምና እምነት ተከታዮችና የክርስትና እምነት ተከታዮች የበለጠ መተሳሰር እንዳለባቸው፣ የሁላችንም አገር የሆነችውን ኢትዮጵያ የየግል ሃይማኖታዊ እምነታችንን ይዘን፤ የጋራና ታሪካዊ የሆነውን ሰንደቃችንን በጋራ አነግበን ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ መብት የሆነውን ዘረኛና ጐጠኛ የሆነውን ገዢ ቡድን መታገል እንዳለብን አሳስበወል። በተለይም የእሥልምና እምነት ተከታይ ወገኖቻችን ባነሱት የመብት ጥያቄ ላይ ውዥንብር ለመፍጠር ወያኔና በባዕዳን የሚደገፉ ስብስቦች የሚነዙትን ውዥንብር በተባበረ ኃይላችን ማጥራት የሁላችንም ግዴታ እንደሆነ አሳስበዋል። የሰብዓዊ መብት ጥያቄ፣ ካለህግ የታሰሩና ደብዛቸው ከጠፉ ዜጐች ጋር ወግኖ ለፍትዕ መቆም አገራዊ ብቻ ሳይሆን አለም አቀፍ ግዴታም እንደሆነ አስረድተዋል።



አቶ አሊ በዚሁ ግብኝታቸው ወቅት በስዊድን ሀገር የሚኖሩትንና በሕዝባዊ

ብዕራቸው የሚታወቁትን ታላቅ የጥበብ ሰው ገሞራውን አግኝተው ጭውውት አድርገዋል።

ከዚህ ባሻገርም በወያኔ ጕጠኛ ቡድን ከአመት በላይ ታስረው የነበሩትን



ሁለት ስዊድናዊ ጋዘጤኞች (Mr· Johan Persson and Martin Schibbye) በግል በመገናኘት በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት ረገጣና የፖለቲካ እስረኞችን ሁኔታ በዝርዝር አስረድተዋል። እነዚህ ጋዜጠኞች በወያኔ እስር ቤት በነበሩበት ወቅት SOCEPP የነሱን ካለፍርድ በእስር ቤት መማቀቅ፣ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ስለሆነ፣ በዛ ወቅት እነሱን አስመልክቶ ፍትሃዊ ፍርድ እንዲያገኙ SOCEPP ያደረገውን የተመዘገበ ጥረት አስረድተዋቸዋል። እነዚሁ ጋዜጠኞች እራሳቸው ካዩት መከራ፣ በሌላም መንገድ ባሰባሰቡት መረጃ በኢትዮጵያ ስላለው የሰብዓዊ መብት ረገጣና የፍርድ ሥርዓት መደፈር በተለይም የፖለቲካ እስረኞችን አስመልክቶ ያለውን ሁኔታ በቂ ግንዛቤ እንዳላቸው በመግለፅ፣ ይህንን ሁኔታ ለስዊድን ህብረተሰብ ለማስረዳትም ሆነ ዓለም አቀፍ ግንዛቤ እንዲያገኝ ከ SOCEPP ጋር በመተባበር የተቻላቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ከሚቴ ሊቀመንበር አቶ ዓሊ ሁሴን በስቶክልም ቆይታቸው፣ ታዋቂ የሆኑ የሰብዓዊ

መብት ተቆርቋሪ ግለሰቦችን አነጋግረዋል። የክርስትናና የእስለምና ተከታይ ወገኖቻችንን ጊዜ በመውሰድ፣ አገራችን በአጠቃላይ ስላለችበት ሁኔታ አወያይተዋል። በተጨማሪም SOCEPP በሰብዓዊ መብት አኳያ እያደረገ ያለውን ጥረት በዝርዝር አስረድተዋል። የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያዊን በተጣመረና በተባበረ ትግላቸው የወያኔን የመከፋፈል ሤር እንዲያከሽፉ፣ በአጠቃላይም በዲያስፖራው የሚኖረው ዜጋ ሁሉ፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ወገኖቻችን ያነሱትን የመብትና የእምነት ጥያቄ በመደገፍ፣ በሃገራችን እየተካሄደ ያለውን ሁለገብ የመብትና የዲሞክራሲ ትግል እንዲቀላቀሉ አሳስበዋል።

በአጠቃላይ አቶ ዓሊ ሁሴን፣ በስዊድን አገር ባቻ ሳይሆን በተለያዩ የኤውሮፓ አገሮችም እየተዘዋወሩ ያደረጉት የሥራ ጉብኝት፣ ለቀጣዩ ትግልም ትልቅ መሠረት የጣለና ኢትዮጵያዊን ላጠቃላይ የመብትና የዲሞክራሲ ትግል በህብረት መቆም እንዳለባቸው ከፍተኛ ግንዛቤ ጥሎ ያለፈ መሆኑ ግልፅ ነው። ስለዚህም ሁላችንም በያለንበት ይህን መሰል ጠቃሚ መሠረት ላይ በመቆም ባደረጉት አስተዋፅዖ ላይ የበለጠ በመገንባት፤ ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ መብት የሆነውን የወያኔን ዘረኛና ጐጠኛ ቡድን ዕድሜ በማሳጠር ውድ አገራችንን እንድንታገድ የበኩላችንን ጥሪ እናስተላልፋለን።

ሞት ለወያኔ! ድል ለኢትዮጵያ ሰፊው ህዝብ!!